ፓኖራማ ቁጥር 50

**የትዝብት አድማስ**

**ህዳር 5 ቀን 2001 ዓም**

## <u>አምባገነን ሥርዓት በሕዝባዊ አመፅ እንጅ</u>

## <u>በልመና አይወገድም</u>

ከዓለም ሕዝቦች ታሪክ መማር ከተፈለገ፥ በዘመናት አምባገነኖች ከሥልጣናቸው የሚወርዱት፥በሕዝብ መራራ አመፅና ባልተቋረጠ ትግል መሆኑን ነው:: በደልና ግፍ፥ ስቃይና መከራ፥ ጭቆናም ይሁን የፍትህ-ርትዕ መጓደል ሲኖር፥ ሰብዓዊ ፍጡር ቀርቶ፥ አራዊትና እንስሳትም ማመፃቸው የተፈጥሮ ሕግ ነው:: እሳት ከሌለ ጭስ አይኖርም እንደሚባለው፥ በደልና ግፍ ከሌለ አመፅ ሊኖር አይችልም:: በመሆኑም፥ የአመፁ ሁሉ ምንጩና ምክንያቱ፥ ያው ዞሮ ዞሮ በደልና ጭቆና ነው:: ፍትኅ-ርትዕ ካለ፥ ዳኝነት ካልተጓደለ፥ አስተዳደር ከተስተካከለ፥ ሙስና ከሌለ፤ የፖለቲካውና የኢኮኖሚው ሥርዓት የሕዝብን መብት የሚያስከብርና መሠረታዊ ፍላጎቱን እንዲያረካ ሆኖ ከተዋቀረ፥ ሕዝብ ለአመፅ ብቻ አምፃለሁ ብሎ የተነሳበት አጋጣሚ መኖሩን አናስታውስም:: ከሞላ ጎደል፤ ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ ከተሟሉለት፥ ቅድሚያ የሚሰጠው፥ ሠላማዊ ሕይወቱን እየመራ ቤተሰቡን መርዳት፥ ኑሮውን ማሻሻል፥ ልጆቹን ማሳደግና መልካም ዜጋ እንዲሆኑ መጣር ነው:: ለአመፅና ለመስዋዕት ሲል ብቻ ጊዜውንና ሕይወቱን የሚገብርበት ቅንጦትና ፍላጎት አይኖረውም:: ሕዝብ በጀብደኝነት ብቻ ተነሳስቶ ለማመፅ የሞከረበት አጋጣሚ ትዝ አይለንም::

ይህን የኅብረተሰብ መሠረታዊ ፍላጎትና ምኞት ባለመረዳት ነው ሁል ጊዜ፥ አምባገነኖች ሕዝብን እየጨቆኑ፥ እየበደሉ፥ ግፍና ስቃይ እያበዙበት ወደ አመፅ ትግል የሚገፋፉት:: አመፅን ለማስወገድ በግድ የጭቆናንና የበደልን ምንጭ ማድረቅ አማራጭ አይኖረውም:: ያ ካልሆነ፥ ሕዝባዊ አመፅ አይቀሬ ነው:: እስካሁን በታሪክ እንደታየው ከሆነ ደግሞ፥ የሕዝብን አመፅ የሚገታው ኃይል አልተገኘም:: ታዲያ፥ የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠ ማነኛውም ኃይል ቢሆን ፤ ማድረግ የሚገባው፤ ሕዝብን ከመበደልና ከመጨቆን መቆጠብ ያለበት መሆኑን ነው:: ሠላምን የሚፈልጉ ሁሉ፥ ሠላም የሚገኝበትንና የሚሰፍንበትን ሁሉ ማድረግ አለባቸው:: በየትኛውም ወገን ቢሆን፥ ሠላም እንዳይገኝ ምክንያት የሚሆኑትን ክስተቶች ሁሉ፥ በነባቢትም ሆነ በድርጊት መፈፀም አይኖርባቸውም:: ሠላምንና መረጋጋትን ፥ ከሕዝብ የበለጠ የሚፈልግና የሚመኝ አይኖርም:: ምክንያቱም፥ሠላም ከሰፈነ፥ ወደ ልማቱ፥ ዕድገቱና በኑሮው ማሻሻል ላይ ለማተኩር ስለሚፈልግ ነው:: የሠላምን ጥቅምም ሆነ የጦርነትን አጥፊነትና ጎጅነት ከሕዝብ የበለጠ ማንም ሊረዳው አይችልም::

*ምክንያቱም፥ ሰላም ደፍርሶ ጦርነት ሲመጣ በቅድሚያና ከማንም በበለጠ በቀጥታ የሚጎዳው ሕዝቡ ስለሚሆን ነው። በመሆኑ፤ በየጊዜው ሠላም የሚነሱትን፥ ሁሉ ይቃወማቸዋል። "ወተት ይሸፍታል እንጂ ሰው ሲበደል" የሚለውም ቅኔ ሊቀኝ የበቃውም፥ ባላገር በመንግሥት ላይ ከአመፀ፥ ከመሸፈት የሚያግደው የለም የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ፥ አመፅ ዕንግዳ አይሆንበትም። መሳሪያ እያነሳ የውጭ ወራሪ ኃይሎችን በየጊዜው እንደተዋጋቸው ሁሉ፥ የሀገር ውስጥ ጨቋኞችንም፥ በተመቸው የትግል ስልት ሲቃወማቸው ኖሯል። ዛሬም ይሁን ወደፊት ይህንን ከማድረግ የሚያግደው አይኖርም። ችግሩ ግን፥ ተፈራራቂ አምባገነን ገዥዎቹ ይኸንን ሀቅ መቀበል አለመፈለጋቸው ነው። ይህን ሀቅ እስካልተቀበሉ ድረስ ደግሞ በሕዝባዊ ኃይልና ትግል መወገዳቸው አይቀርም። ምን ጊዜም ቢሆን፥ ሠላምን ሳይፈልጉ፥ ሠላምን የሚሹ ሁሉ፥ ሠላምን ጭራሽ ሊያገኟት አይችሉምና ነው። አንተ ሰላም እንዲኖርህ ከፈለግህ ጎረቤትህን ሰላም አትንሳው የሚባለው፥ አላስፈላጊ የሆነ መተናኮል የአጋንንት በረት ይከፍትና አንተም በጤና ልትኖር አትችልም ለማለት ነው። አምባገነኖች የሚገዙትን ሕዝብ ሰላም ስለሚነሱ በሕዝብ አመፅ ይደመሰሳሉ እንጂ በሰላም መግዛት አይችሉም።*

*አምባገነኖች፥ እነርሱ ራሳቸው የአመፅ ምንጭ ሆነው እያሉ፥ ብሎም፥ የሠላም አለመገኘትና ያለመረጋጋት ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው ሳሉ፥ የሕዝባዊ አመፅ ምክንያት፥ ሌሎች ናቸው በማለት እራሳቸውን ያታልላሉ። ወደ ሀገር ቤት የሚገባው የውጭ ዕቃ ዋጋው ሊወደድ የበቃው፥ ኢሕአፓ የሚባለው ድርጅት፥ የሲውዝ ካናልን የመርከቦች መተላለፊያ የባህር በር ስለዘጋው ነው ብለው በዘመነ ደርግ የነበሩ ከንቱ አማካሪዎች አስቂኝ ቧልት እየደረደሩ የሕዝባዊ-ሠላማዊ አመፅ ምክንያትም ይኸው ድርጅት ሳይሆን አይቀርም በማለት ይቃዡ ነበር። ዛሬም ወያኔዎቹ ከዚህ የፍርኃት ቅዠት ነፃ ሊወጡ አልቻሉም። ዛሬም እንደትላንቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቦታው ወያኔን በመቃወም በሚያደርገው ሕዝባዊ አመፅ፥ የአመፁ ምክንያትና ምንጩ ኢሕአፓ ነው ለማለት ይከጅላቸዋል። ይህን ቢሉም ግን ምክንያት አላቸው። ምክንያቱም፥ኢሕአፓ፥ ከማንም በበለጠና በተሻለ የወያኔዎቹን እኩይ ባኅርይና አጥፊ ተግባር በማያሻማ መንገድ፥ እየተከታተለ ለሚታገልለት የኢትዮጵያ ሕዝብ መግለጹ ብቻ ሳይሆን፥ ሀገሩንም ከወያኔ የዘር አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በቁርጠኝነት ታጥቆ የቆመ በመሆኑ ነው። ታዲያ፥የወያኔ መሪዎች፥ኢሕአፓን "ለማጥፋት"ያዙን ልቀቁን ቢሉ አይፈረድባቸውም። በአጥፊና ጠፊ ሥነ አዕምሮ ውስጥ ራሳቸውን ሸብበው ስለሚኖሩ፥ እስከ ፍፃሜ ህይወታቸው ድረስ የአዕምሮ ሰላምን አያገኙም። ኢሕአፓን "ካላጠፉ" የሰላም እንቅልፍ እንደማያገኙ በሚገባ ያውቁታል። ሐቁ ግን ወያኔዎቹ ይጠፏታል እንጅ፥ ኢሕአፓ እንደሆን አይጠፋላቸውም! ደርግም ሞክሮ አልተሳካለትምና!!!*

*በመጀመሪያ ደረጃ፥ የተጨቆነ፥ የተበደለ፤ የከፋውና የወያኔ ሥርዓት የከረፋው ሕዝብ፥ የማንንም ቅስቀሳና ጉትጎታ የሚያስፈልገው አይደለም። ለወያኔ መሪዎችም አቤት ወዴት ብሎ ሊገዛላቸው አልቻለም/ አይችልምም።*

*ይህ አሁን በኢትዮጵያ ያለው የፖለቲካ ሐቅ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ÷ ኢሕአፓም ይሁን ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች÷ በወያኔ አገዛዝ ላይ አምፀው በመታገል ላይ የሚገኙት ወድደው ሳይሆን÷ ተገድደው ነው:: ሕዝቡም በየቦታው የሚያምፀው÷ የወያኔ የዘር ፖሊቲካ ሥርዓት ስለአንገፈገፈው እንጅ ጠብ ያለሽ በዳቦ በሚል እሴት አይደለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ከአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ጀምሮ መራራ መስዋዕት በመክፈል የመለስ ዜናዊን ቡድን የዘረኛ ሥርዓት በመቃወም ላይ መገኘቱ÷ የተገፈፈውን መብቱን ለማስመለስና ብሔራዊ ነፃነቱን ለማስከበር ብቻ ነው:: ኢሕአፓም በልሳኑም ይሁን በሌሎች መግለጫዎች የሚያወጣቸው ሕዝባዊ ጥሪዎች በሙሉ÷ የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት በማድረግ ብቻ ነው:: ይህም ዕምነቱ፤ አምባገነኖች ያለ ሕዝባዊ አመፅ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለሕዝብ ያስረክባሉ የሚል ቅዠትም ይሁን ብዥታ ኖሮት ስለማያውቅ ነው:: እነ መለስ ዜናዊን ለመቃወምና ከሥልጣናቸው ለማስወረድ የእነርሱን ሕግና ደንብ በመከተል ብቻ ነው የሚለውን ብዥታ የሚያስተናግዱትን ሁሉ÷ ምናልባት ያሳዝኑት እንደሁ እንጅ ዕምነታቸውን ይገነዘብላቸዋል:: በዴሞክራሲ ሂደትና አሰራር ስለሚያምን÷ የሌሎችን የተሳሳተ ዕምነት ባይቀበልም ያከብርላቸዋል:: ኢሕአፓን ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ከሚያስተሳስሩት መሠረታዊ አቋሞቹ መካከል÷ በሕዝባዊ አመፅ አምባገነኖችን አስወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መተካት አንዱና የመጀመሪያው ነው:: ይህንን ዓይነተኛ የትግል መርሆ በማንገብ ከወያኔ በፊት የነበሩትን ሁለት አምባገነን ሥርዓቶች አይከፍሉ መሥዋዕት እየከፈለ ታግሏቸዋል::አሁንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመሰለፍ÷ ዘረኛውን የመለስ ዜናዊን ቡድን እየታገለው ነው:: የዴሞክራሲ ሥርዓት እስኪሰፍን ድረስም÷ እየታገለ ያታግላል:: ዛሬም እንደትላንቱ የሚጠበቅበትን መሥዋዕት በመክፈል ሕዝባዊ ወገንተኝነቱን በተግባር ያስመሰክራል:: ይህ ሐቅ ደግሞ÷ ምሥጢረ – ወያኔ ሳይሆን÷ የትግላችን ሀሁ÷ የዓላማችን አቡጊዳ÷ የራዕያችንና የግባችን አለፋና ኦሜጋ ነው:: ይህን ክስተት ደግሞ እንኳን የምንሰዋለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ የወያኔ መሪዎችና አሳዳሪዎቻቸው ሳይቀሩ÷ በሚገባ ያውቁታል:: በእኛ ዕምነት÷ የአምባገነን ሥርዓት÷ ንጉሣዊ ካባ ይጎናፀፍ÷ ወታደራዊ ጃኬት ይደርብ÷ እንደ ኢራን ገዥዎች የሃይማኖት ድግ ያገልድም÷ ወይም እንደነ መለስ ዜናዊ የብሔር ጥብቆ ያጥልቅ÷ ያው ፀረ ሕዝብና ሀገር አጥፊ ነው:: ለዚህም÷ ከነመለስ ዜናዊ ቡድን የበለጠ ማስረጃ አያስፈልገውም:: የመለስ ዜናዊ ቡድን የብሔር ድርጅትን እወክላለሁ በማለቱ ብቻ÷ የተለየ እንክብካቤና እሽሩሩ ሊባል አይገባም:: ይህንን ዳንኪራ ከሚረግጡት ጋር ጎራችንን አናደርግም:: ሰልፋቸውም ሰልፋችን አይሆንም:: የትግላችን ዓላማና ግብ÷ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆሞ÷ አምባገነኖችን ለመታገልና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በሚደረገው ትግል የበኩላችን ሀገራዊ ድርሻ ለመወጣት እንጅ÷ የአምባገነኖችን ላባ ለማርገብ አይደለም:: የመለስ ዜናዊን ሀገር አጥፊ ቡደን የምንቃወመውም ከዚህ መተከላዊ ዓላማ በመነሳት ነው::*

*ወያኔዎቹም ይህንን የማይበገር÷ የማይውገረገርና ለድርድር የማይቀርብ የፓርቲዉን አቋም÷ ማንም ሳይነግራቸው በሚገባ ያውቁታል:: ከዚህም*

በመነሳት ይመስላል፥ መለስ ዜናዊ ፥ ኮር አባላት ለሚላቸው ተከታዮቹ ባስተላለፈው የምሥጢር መመሪያ ( ሰርኩላር) “የአማራ ምሁራንና ተራማጅ ክፍሎች፥ መሬት ላራሹ፥ የብሔሮች እና የሃይማኖት እኩልነት፥ ዴሞክራሲ ወዘተ እያሉ በራሳቸው መንግሥትና ሥርዓት ላይ በማመፅ፥ የእነርሱ ሥርዓት በመንኮታኮቱ እኛ ባመጣነው ጣጣ ዛሬ ጉድ ሆንን እያሉ፥ እንደሚናደዱት ሁሉ፥ እናንተም አሁን ዴሞክራሲና የኢትዮጵያ አንድነት እያላችሁ በራሳችሁ መንግሥት ላይ ለማመፅ ከሌሎች ጋር እንተባበር የምትሉትን አደገኛ ነገር ማቆም አለባችሁ። እኛ ከወደቅን በኋላ እናንተ ነገ እንደነርሱ ትፀፀታላችሁ።” የሚል መልዕክት እንዳስጨበጣቸው ለማወቅ ተችሏል። የዚህን መልዕክትና መመሪያ ትርጉም፥ የሚያስከትለውንም አንደምታ መዘርዘር የለብንም። ወያኔዎቹ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በኩል የማይቀርላቸውን ቁጣ ለመከላከል የማያደርጉት ዘዴና መሰናዶ እንደማይኖር ምን ጊዜም ቢሆን ልንዘነጋው አይገባንም። ምንም ምን መሰናዶ በማድረግ፥ የመከላከል ዝግጅትና ምሽግ ቢቆፍሩ፥ ከታሪክና ከሕዝባዊ ፍርድ ማንም እንደማያድናቸው ማወቅ ነበረባቸው። በመሆኑም በቆፈሩት ጉድጓድ ይቀበሩበታል እንጅ ኢትዮጵያና ዜጎቿ ግን አሁን ካጋጠማቸው የጥፋት አደጋ እንደሚድኑ እነርሱም ይሁኑ ሌሎች ጠላቶቻችን ሊረዱት ይገባል። በአምባገነን ሥርዓት ላይ አምጾ መነሳት፥ ሰብዓዊ መብትን ማስከበር ብቻ ሳይሆን፥ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ከጥፋት ለማዳን ቆርጦ መነሳት፥ ታሪካዊ ተልዕኮና ብሔራዊ ግዴታም ጭምር መሆኑን ማንኛው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ አውቆ ተረድቶ ወቅቱን በመጠባበቅ ላይ ነው!!!! በደልና ጭቆና አመፅን ስለሚቀፈቅፉ፥ ሕዝባዊ አመፅ ደግሞ ጭቆናን ለማስወገድና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት፥ በፋና ወጊነት ወሳኝ ሚናን ይጫወታል !!!!